ሁሉም ማለትም መለስም፣ ተወልደም፣ ገብሩም ስዬም፣ ስለትግራይ ያላቸው ራእይ ተመሳሳይ ነው። ያጣላቸውም እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እንጂ ሌላ ምንም አይደለም። ለዚህምነው አንዳቸው ህወሀት ሌላኛውን ህወሀት አሸንፈው የተቀረው አሸናፊውን ሕወሀት ተቀብሎ አሜን ብሎ የሚኖረው። አሁንም አንገታቸውን የደፉት እነ ስዬ አንድም ቀን አምልጧቸው የሕወሀትን ጥፋት የተናገሩበት ቀን ትዝ አይለኝም። የተወሰነ ቡድን ላይ ነው ግግም ያሉት። አሁን ባለው ሁኔታ በዋንኛነት የኢትዮጵያ ችግር ማእከል ያደረገው እዚያው እ ትግራይ ወይንም ከትግራይ የወጣው ሕወሀት ላይ ነው

--------------------// ------------------

“ባለሙያና ስራ ያልተገናኙበት አገር ዜጎች ነን” ….ባለሙያና ስራ ብቻ አይደለም አዋቂና ተገቢ ሰዎች በተቢው ቦታ የማይሾሙበት አገር። የህክምና ባለሙያ የመንገድ ስራ ባለስልጣን ሀላፊ ሆኖ የሚሾምበት ብቻ አይደለም፤ የሽምቅ ተዋጊ የአገር መሪ ሆኖ የሚቀመጥበት

------------------//--------------------------

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበርን ሰዎች እስከምናውቀው ድረስ ይኸ ሰው ከማንም የኢህአዴግ ግልገል ካድሬዎች በላይ የሚያምንበትን ሲፅፍ ኖሯል። የህዝብ አለኝታ በሆኑ ምሁራንና የህዝብ አንደበት በሆኑ የነፃ ውፕሬስ ውጤቶች ላይ ያለ አንዳች ገደብ ተሳልቆባቸዋል። በሥልጣንና በካድሬነት ሥራ ዘመኑ ከ”ይበልታ” በስተቀር ማንም በክፉ ዓይን ያየው የመንግሥት ሹም አልነበረም። እርሱ በመጽሐፉ ውስጥ ባይጠቅሰውም በአንድ ወቅት ”የፕሬስ ሕግን በመተላለፍ” ተብሎ ክስ ተመስርቶበት ከእኛ ከነፃ ውፕሬስ ጋዜጠኞች ጋር ልደታ በሚገኘው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተከሳሽ ሳጥን ውስጥ ቆሞ ተመልክቼዋለሁ። በእርሱም ቢሆን ምንም የደረሰበት ቅጣት አልነበረም። ቀድሞውኑም ”እፎይታም ይከሰሳል” የሚል ድራማ በእኛ ላይ ለመሥራት ነበርና።

## ተረግጠህ ተገዛ
## ወይ ክንድህን አንሳ

ሰምቶ ፣ ዝም<br>
ሰምቶ፣ ዝም<br>
በሆድ ያለ አይነ ቅዝም፣<br>
ሲሉህ አብረህ አታዝግም፣<br>
እያስተኙህ ነው በህልም።

አዎን ማለት መረታት፣<br>
አለመጠከት መመታት፣<br>
እንዳሉት አበው በመጻፍት፣

ከጉዋዶችህ ጋር ሰነባብት፣<br>
ምከር በጋራ በቀናት፣<br>
በህግ አራዊት ሥርዓት፣<br>
ላለመገዛት በህወሀት፣<br>
ክንድህን አንሳ በሰዓታት።<br>
ጊዜ አትስጣቸው ሳምንታት።

አሊያ ወይ ለራስህ ነጻነት ስትል ታገል፣
አለበለዚያ እንደወደል አህያ ተረግጠህ ዝምበል፣
አታሳድፍ ወኔያቸውን መንፈሳቸውን አትበክል፣
የጀግኖች አባቶችህን አጽሞች አታበራይ አታንግዋልል፣

ቡከን!ለራስህ አልቅስ በቁምህ እያበላህ ተዝካርክን፣
ከገዳይህ ፊትፍት የውርደት ፍትፍት ዘካህን፣
ይልቅስ ….ይልቅስ …መክተህ ግደል የማይተውህን፣
ተንበርክከህ ከመኖር የውርደት ኑሮ ዘመንክን።

ይህ ግጥም ለቀድሞየቅንጅት መሪዎች መታሰቢያ የቀረበ የነበረ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ ተስተካክሎበቅርቡ በወያኔ የፈጠራ ክስ እስር በት ለተወረወሩት ወገኖቻችንና እንዲሁም፣ ከዝህ በፊትም በወያኔ ለተወረወሩት ጀግኖች ወንድሞቻችንና፣ እህቶቻችን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የተበረከተ ግጥም ነው

እንግዳ ታደሰ ሚያዝያ 20/2001